አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

፮ኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th year No.57
Addis Ababa 19th December 2014


**ማውጫ**


**የአዲስ አበባ ከተማ የውሻ ዕብደት በሽታ ደንብ…………………………………………ገጽ ፮፻፺፬**


**CONTENTS**


**The Addis Ababa City Rabies Regulation……....................…page 694**


## ደንብ ቁጥር ፶፯ /፪ሺ፯

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ

በአዲስ አበበ ከተማ የውሻ ዕብደት በሽታ ክስተትና ስርጭት ከምንጊዜም የበለጠ እየተሰፋፋ በመምጣቱ ሰውንና የተለያዩ እንስሳትን በመጉዳት ለሞት በመዳረግ ላይ በመገኘቱ፤

የሰውንና የእንስሳትን ሕይወት ከዚህ አደገኛ በሽታ ለመታደግና የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የውሻ እብደት በሽታ መከላከያ ክትባት መስጠት፣ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ በአንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## Regulation No.57/2014

## A Regulation to Provide for the Prevention and Control of Rabies in Addis Ababa City Government

**WHEREAS,** it has been found that in Addis Ababa City the disease of rabies has been increasing at high rate and magnitude than at any time and this has been causing death to human being as well as various animals;

**WHEREAS,** it has been found necessary to provide rabies preventive vaccination to save human as well as animal life from this dangerous disease;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No 361/2003 and Article 84 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No 35/2004 the City Cabinet has issued this Regulation as follows.


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር ፶፯/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩.**"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

፪.**"አግባብ ያለው ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ወይም በቢሮው የተወከለ አካል ነው፤

፫.**"ክፍለ ከተማ"** ማለት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፪(፭) የተመለከተው የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፬.**"ወረዳ"** ማለት የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፭.**"እንስሳ"** ማለት ለዚህ ደንብ ዓላማ ሲባል የቤትና የዱር እንስሳትን ያጠቃልላል፤

፮.**"ለውሻ ዕብደት በሽታ የተጋለጠ"** ማለት በበሽታው መለከፉ የተረጋገጠ ወይም በተጠረጠረ ውሻ የተነከሰ፣ ወይም ሌላ ቀጥታ ግንኙነትና ንክኪ የነበረው ሰው ወይም እንስሳት ነው፤

፯.**"በሽታው የተከሰተበት አካባቢ"** ማለት የውሻ እብደት በሽታ የተገኘበት ወይም መኖሩ የተጠረጠረበት አካባቢ ነው፤

፰.**"የውሻ ምዝረባ ሠርቲፊኬት"** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈቀድና አግባብ ባለው ባለስልጣን ለውሻው ባለቤት የሚሰጥ የምዝገባ ሰርቲፊኬት ነው፤



## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "A Regulation to Provide for the Prevention and Control of Rabies in Addis Ababa City Government Regulation No 57/2014".

### 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1. "**Bureau**" means the Addis Ababa City Government Trade and Industry Development Bureau ;
2. "**Appropriate authority**" means the Addis Ababa City Government Trade and Industry Development Bureau or an entity delegated by it;
3. "**Sub-City**" means the second administrative stratum of the City mentioned under Article 2(5) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No 361/2003;
4. **"Wereda"** means the third administrative stratum of the City, which is a unit of Sub-City;
5. "**Animal**" means for the objective of this Regulation, it includes domestic and wild animals;
6. "**Rabies infected**" means a person or animal infected with rabies bitten by a suspected dog, or having direct contact with the suspected dog;
7. "**Infected area**" means a location where the rabies is found or suspected to be found;
8. "**Dogs registration certificate**" means a certificate of registration to be issued to the owner of a dog by the concerned authority as per this Regulation;

፱.**“የውሻ ባለቤት”** ማለት በግል ወይም በጋራ የውሻ ባለቤትነት ማስረጃ ሠርተፊኬት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲.**“ተልከስካሽ ውሻ”** ማለት ባለቤት የሌለው ወይም ከውሻው ባለቤት ቅጥር ግቢ ውጪ በመንገድ ላይ በሌላ ሰው ይዞታ ወይም ለውሻ ባልተፈቀደ ሥፍራ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ እና በመሳሰሉት ቦታዎች ሲዘዋወር የተገኘ ነው፤

፲፩.**“የመከላከያ ክትባት”** ማለት የተዳከመ ወይም ሕይመት የሌለው የበሽታ መንስኤ ተህዋሲያን ውጤት ሆኖ ለጤነኛ እንስሳት በመርፌ የሚሰጥና እንስሳትን ከበሽታ የሚከላከል ነው፤

፲፪.**“የእንስሳት ጤና ባለሙያ”** ማለት በየደረጃው የሚሰጠውን እንስሳት ሕክምና ትምህርት ተከታትሎ በሠርተፊኬት፣ በዲፕሎማ፣ በዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ደረጃ ያለውና ሙያውን ለመተግበር የተፈቀደለት ሰው ነው፤

፲፫.**“የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሠራተኛ”** ማለት በየደረጃው የሚሠጠውን አነስተኛ የቤት እንስሳትን እንደ ውሻ፣ ድመት እና የመሳሰሉትን ተከታትሎ ለመያዝና ለማስወገድ በቢሮው የተመደበ ሥራውን ለመተግበር የተፈቀደለት ሰው ነው፤

፲፬.**“ማምከን”** ማለት ውሾች በቀዶ ጥገና እንዳይወልዱ ማድረግ ነው፤

፲፭.**“የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ”** ማለት ደረጃውን ጠብቆ የተሰራ ለማነኛውም እንስሳት ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ነው፤

፲፮.**“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፯.በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫ . <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ የውሻ ባለቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡



9. “**Dog owner**” means any person issued with certificate of dog ownership in his private capacity or jointly;
10. **“Roaming dog”** means ownerless dog, found to roam out of its owner’s compound or dogs found in possession by another person or in a restricted site for dog, waste disposal site and similar places;
11. “**Vaccination**” means an injection administered for prevention of animal disease which will be transmitted from an infected animal to healthy ones;
12. **“Animal health expert”** means a person who attend veterinary education either at certificate, diploma, degree or above level and authorized to practice the profession;
13. “**Animal health service Staff**” means a person; appointed by the Bureau and accredited to implement the work in order to follow up, keep and avoid smaller domestic animals such as dog, cat and similar in different levels;
14. “**Castration**” means sterilizing dogs through medical surgery;
15. “**Animal health service provision**” means a location for rendering medication service to any animal by keeping the standard of service to this purpose;
16. “**Person**” means any natural or legal person;
17. Unless otherwise expressed, in this Regulation expressions stated in the masculine gender shall apply to the feminine gender.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable on dog owners within the boundary of Addis Ababa City Government.

## ክፍል ሁለት

## የውሻ መዝገብ ስለማቋቋምና ስለመመዝገብ

### ፬. የውሻ መዝገብ ስለማቋቋም

የሚከተሉት የውሻ መመዝገቢያ መዛግብት ተቋቁመዋል፡-

፩.በቢሮው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት የሚተዳደር ከተማ አቀፍ የውሻ መመዝገቢያ መዝገብ፤

፪.በየወረዳው የንግድና እንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ወይም በወረዳ የከተማ ግብርና አስተባባሪ የሚተዳደር የውሻ መመዝገቢያ መዝገብ፡፡

### ፭. በውሻ መመዝገቢያ መዝገብ ስለማስመዝገብ

፩. ማንኛውም ሰው ውሻውን ሳያስመዘግብ የውሻ ባለቤት መሆን አይችልም፤

፪. ማንኛውም ሰው ውሻውን የሚያስመዘግበው በሚኖርበት ወረዳ ይሆናል፤

፫. ማንኛወም ሰው ውሻውን የሚያስመዘግበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤

፬. የውሻ ባለቤት የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ ቀድሞ ላስመዘገበበት የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት በማሳወቅ ወደ አዲሱ አድራሻ ደብዳቤ በመውሰድ እና በማሳወቅ ማስመዝገብ አለበት፡፡

### ፮. ስለ ምዝገባ ማመልከቻ

፩. ማንኛውም ሰው የውሻ ባለቤት መሆን ከፈለገ ወይም ቀደም ሲል የውሻ ባለቤት ከሆነ በቢሮው የሚዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና አስፈላጊውን ማስረጃ በማያያዝ ለወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

፪. የውሻው ባለቤት የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ በቢሮው የሚዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡



## PART TWO

## Establishment of Dog Register and Registration

### 4. Establishment of Dog Register

The following registers of dog are hereby established:

1. Register of dog registration to be administered by the Bureau urban agriculture core business process ;
2. Register of dog registration to be administered by Trade and Industry Development Office of the Wereda or Wereda urban agriculture coordinator.

### 5. Registration in the Dogs Register

1. No person can be the owner of the dog without registering it;
2. Any person shall register his dog in the Wereda he resides;
3. Any person shall register his dog only once;
4. When the owner of the dog changes his address shall consequently notify to the Wereda Trade and Industry Development Office which effect registration previously; and shall bring a letter, notify and register in the new address.

### 6. Application for Registration

1. Any person desiring to be an owner of a dog or previously owned a dog shall fill the application form prepared by the Bureau by annexing appropriate evidence and submit to the Wereda Trade and Industry Development Office.
2. A dog owner who changed his residence shall fill up a form prepared by the Bureau within two weeks of the occurrence and submit to the Wereda Trade and Industry Development Office.

፫. ለመዝገብ የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት በቢሮው ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ የውሻ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት የቀረበለት የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ሲያረጋግጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

**፯. <u>የምዝገባ መረጃዎቹንና ሰነዶችን ስለማስተላለፍ</u>**

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የውሻ ባለቤትነት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዝገባ መረጃዎቹን ወዲያውኑ ለክፍለ ከተማው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ያስተላልፋል፤ ክፍለ ከተማውም ወዲያውኑ ለቢሮው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

፪. የቢሮው ከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የተላለፉትን የምዝገባ መረጃዎች በከተማ የውሻ ባለቤት መዝገብ መዝግቦ ይይዛል፡፡

**፰. <u>ከመዝገብ ስለመሰረዝ</u>**

፩. የውሻው ባለቤት ሲሞት የሟች ወራሾች በሟች ባለቤትነት የተመዘገበው መዝገብ እንዲሰረዝላቸው ለመዘገበው ወረዳ ማመልከቻ ሲያቀርቡ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውራሾቹ የውሻው ባለቤት መሆን ከፈለጉ የተስማማበትን የስምምነት ውል ለወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ካቀረቡ በውሉ መሠረት የውሻው ባለቤትነት ምዝገባ ይካሄዳል፡፡

3. When the application submitted for registration is found acceptable the Wereda Trade and Industry Development Office shall issue certificate of dog ownership to the owner after reciving the payment fixed for the service by the Bureau.
4. The Wereda Trade and Industry Development Office confirm that the presented dog ownership registration application is unacceptable inaccordance with sub-article 1 and 2 of this Article shall consequently notify to the applicant in written by stating its ground of refusal.

**7. <u>Forwarding of Information and Documents Relating to Registration</u>**

1. Any wereda Trade and Industry Development Office making register of dog ownership in accordance with this Regulation shall immediately transfer the entries in the registration through the form prepared for this purpose and transfer it to the Sub-City's urban agriculture core business process coordinator; the Sub-City shall also immediately transfer it to the Bureau urban agriculture core business process.
2. The the Bureau uraban agriculture core business process shall register and keep entries in the register transferred as per sub-article 1 of this Article.

**8. <u>Cancellation of Registration</u>**

1. The heirs of a deceased owner of a dog shall apply cancellation of ownership registration to the Wereda Trade and Industry Development Office when the owner of the dog died.
2. Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, when the Wereda Trade and Industry Development Office have been presented with contractual document for ownership of a dog by heirs, the registration shall consequently be made as per the presented contract.

፫. የውሻው ባለቤት ውሻውን አልፈልግም በማለት በጽሁፍ ለወረዳው ሲያመለክት፡፡

፬. ውሻው በመሞቱ ምክንያት የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ከመዘገብ ሲሰርዘው፡፡

**፱.<u>ምትክ የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛወም ሰው ቀደም ሲል ምዝገባ ላከናወነበት ወረዳ በጽሁፍ በማመልከትና አስፈላጊውን ክፍያ በመፈጸም ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

**፲.<u>የውሻ እብደት በሽታ መኖርን ወይም ጥርጣሬ ስለማሳወቅ</u>**

፩.ማንኛውም ሰው በማንኛውም እንስሳት ላይ የውሻ ዕብደት በሽታ መኖሩን እንዳወቀ ወይም ሲጠረጥር ወይም በበሽታው ምክንያት ሞት መከሰቱን እንዳወቀ በአቅራቢያው ለሚገኘው እንስሳት ጤና ክሊኒክ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ወይም ለፖሊስ ወይም ለህዝብ ጤና ተቋም በፍጥነት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም በውሻ እብደት በሽታ የታመመ ወይም የተጠረጠረ ወይም የሞተ እንስሳ ከሰውም ሆነ ከእንስሳት ተለይቶ በርቀት ለብቻው መጠበቅ ወይም መያዝ አለበት፡፡

**፲፩.<u>የውሻ እብደት በሽታ መኖሩን ለማረጋገጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት</u>**

፩. የእንስሳት ጤና ባለሙያ በደረሱት መረጃዎች መሠረት አንድ ውሻ የውሻ እብደት በሽታ የተያዘ ስለመሆኑ መረጃ ከደረሰው በውሻው ላይ ተጨማሪ የማረጋገጫ ምርመራ ሊያካሂድ ወደሚችል አካል ይልካል፡፡

፪.በውሻ ዕብደት በሽታ ተጠርቅሮ ክትትል እየተደረገበት ያለ ውሻ ወይም ሲልከሰከስ የተገኘ ውሻ ቢወገድ የካሳ ክፍያ አይጠየቅበትም፡፡

3. When the owner of the dog submits written request to the Wereda for renouncing ownership on the dog.
4. When the Wereda Trade and Industry Development Office urban agriculture business process cancels the registration due to the death of the dog.

**9. <u>Issuance of Substitute Dogs Ownership Registration Certificate</u>**

Any person who lost or damaged his dog register certificate shall be given the replacement certificate when the person applies to the Wereda he registered priorly in written and by paying the appropriate payment.

**10. <u>Notification Existence or Suspicion of Rabies</u>**

1. Any person knowing or suspecting the occurrence of rabies on any animal or occurrence of death due to the disease shall immediately notify to the nearby animal health clinic or appropriate authority or to the nearby police or public health institution.

2. Any animal which is infected or suspected to be infected by rabies or dead shall be kept at distant separately from humans and animals.

**11. <u>Activities Undertaken to Confirm the Presence of Rabies</u>**

1. As per the information available to him on any dog whih is with rabies the animal health professional shall refer the matter to an entity that can undergo additional diagnosis on the dog.
2. Payment of compensation shall not be claimed when a dog which has been followed up on ground of rabies or roaming has been avoided.

**፲፪.የውሻ ዕብደት በሽታ የተከሰተበትን አካባቢ ይፋ ስለማድረግ**

ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውሻ ዕብደት በሽታ የተከሰተበትን አካባቢ ይፋ በማድረግ በሽታውን ለመቆጣጠር እንዲቻልና እንዳይዛመት ለማረግ በዚህ ደንብ የተዘረዘሩት ተግባራት እንዲፈጸሙ ያደርጋል፡፡

**፲፫.የውሻ ዕብድር በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የውሾቹን እንቅስቃሴ ስለመቆጣጠር**

፩.የውሻ ዕብደት በሽታ የቁጥጥርና የመከላከል ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ ማንም ሰው አግባብ ካለው ባለስልጣን ህጋዊ የማዘዋወሪያ ፈቃድ ሳያገኝ የውሻ ዕብደት በሽታ ከተከሰተበት አካባቢ ውሻን ወደ ሌላ አካባቢ መውሰድ፣ ማዘዋወር ወይም ከሌላ አካባቢ የውሻ ዕብደት በሽታ ወደ ተከሰተበት ቦታ ማምጣት አይችልም፡፡

፪.የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የሚኖር ማንኛውም የውሻ ባለቤት የሆነ ሰው ውሻውን ለብቻው ለይቶ በማሰር መጠበቅ አለበት፡፡

፫.ከውሻው ባለቤት ይዞታ ውጪ ከባለቤቱ ተለይቶ ሲዘዋወር የተገኘ ማንኛውም ውሻ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ባለሙያ ይወገዳል፡፡

**፲፬.በውሻ ዕብደት በሽታ የተጋለጠ ውሻን በቁጥጥር ሥር ስለማዋል ወይም ስለማስወገድ**

፩.የእንስሳት ጤና ባለሙያ የመከላከያ ክትባት መውሰዱን የሚያረጋግጥ መረጃ ያለው ውሻ ከሌላ የውሻ ዕብደት በሽታ ከያዘው ወይም መያዙ ከሚጠረጠር ውሻ ጋር ከተገናኘ እንደገና እንዲከተብና በቁጥጥር ስር ሆኖ ለ ፲ ቀናት ለብቻው እንዲጠበቅና በባለሙያ ክትትል እንዲደረግበት ይወስናል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ዓይነት ጉዳይ ሲያጋጥም የእንስሳት ጤና ባለሙያ ውሻው ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ በአቅራቢያው በሚገኘው የእንስሳት ጤና ክሊኒክ እየቀረበ እንዲታይና ክትትል እንዲደረግበት ይመስናል፡፡

**12. Publicizing Rabies Infected Area**

When it deems necessary the Bureau shall publicize the area of rabies occurrence in order to enable prevention and control of the occurrence by executing the activities listed by this Regulation.

**13. Controlling Movement of Dogs in Rabies Infected Area**

1. When rabies control and prevention task has been performed, any person shall not bring a dog from area of rabies to other areas or transferring from other areas to areas infected by rabies unless getting approval of transfer from the appropriate authority.
2. Any dog owner dwelling in rabies infected area shall separate and maintain his dog in separation from other infected dogs.
3. Any dog which is found to roam around other than the holding of its owner shall be avoided by the appropriate authority or professional.

**14. Controlling or Avoiding a Dog Infected With Rabies**

1. When an animal health professional who have information about a dog confirming as to administration of vaccination when contacting with another dog infected with rabies or suspected to have infected with the diseases shall take measures of controlling for revaccination and sole preservation of the said dog for 10 days together with follow up by profession,
2. When the case mentioned under sub-article 1 of this Article is happened, health professional shall decide for check up of the dog by the nearby animal health clinic at least twice in a month for further follow up.

**፲፭.የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የእንስሳት ውሻን በቁጥጥር ስር ስለ ማዋልና ስለማስወገድ**

፩.አንድ ሰው በተከተበም ሆነ ባልተከተበ ውሻ ቢነከስ የውሻው ባለቤትና የተነከሰው ሰው በአስቸኳይ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የህክምና ተቋም ቀርበው ሪፖርት ማድረግና የመጀመሪያ እርዳታ እንዲያገኝ ማድረግ አለባቸው፤ ሪፖርት የቀረበላቸው የአካባቢ አስተዳደርና ፖሊስ አካላት ሁኔታውን የመከታተል ግዴታ አለባቸው፤ በውሻ የተነከሰ ሰው የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ካገኘ በኋላ በአካባቢው ወደ ሚገኘው ጤና ማዕከል በፍጥነት መወሰድ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም ውሻ የመንከስ ጉዳት ሲያደርስ ባለቤቱ ውሻውን የማስመርመር ግዴታ አለበት፡፡

፫.ውሻው የውሻ ዕብደት በሽታ ምልክቶች የሚያሳይ ከሆነ ባለቤቱ እንዲያወቀው በማድረግ በእንስሳት ጤና ሠራተኛ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፬.ውሻው ጤናማ መስሎ ከታየ ወይም ባለቤቱ እንዲወገድ ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲካሄድበት ካልተስማማ ቢሮው ወይም አግባብት ያለው ባለስልጣን በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ለብቻው አቆይቶ የጤናው ሁኔታ ክትትል ይደረግበታል፡፡

፭.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ክትትል የተደረገለት ውሻ ጤናማ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለቤቱ ውሻውን አስከትቦ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡

፮.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ክትትል ተደርጎለት ጤናማ ያልሆነ ውሻ በባለሙያ ይወገዳል፡፡

**15. Controlling and Avoiding a Dog that Bitten Person, in the Area where Rabies has been occurred**

1. When any person is bitten by a vaccinated or unvaccinated dog, the owner of the dog and the victim shall forthwith appear and report before the nearby medical institution and got first aid service; the Wereda administration and the police before which the matter has been reported shall be duty bound to follow up on the issue; after getting first aid medication a person bitten with a dog shall be consequently taken to the health center in the area.
2. When a dog has caused biting accident, the owner is duty bound to take the dog for diagnosis.
3. When the dog has shown symptoms of rabies, the owner shall be notified and consequently be avoided through animal health professional.
4. When the dog causing biting accident is apparently looking health or suspected to be of unsound health, it shall be independently kept within the period put forth by the Bureau or appropriate authority and also being checked up as to its health condition.
5. As per sub-article 4 of this Article, when a dog which being followed up is found to be healthy, the owner shall get vaccination of the dog for taking delivery of it.
6. A dog which is found to be unhealthy by the medical diagnosis made as per sub-article 4 this Article shall be avoided through a professional.

## ክፍል ሶስት
## ስለ ውሻ ክትባትና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

**፲፮. ስለ ውሻ ባለቤትነት፣ ስለ ውሻ ክትባት የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ውሻን ስለማምከን**

፩.ማንኛውም የውሻ ባለቤት የሆነ ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ መሠረት የውሻው ዕድሜ ሶስት ወር ሲሞላው በሚኖርበት የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት እየቀረበ የማስመዝገብ ፣ የውሻ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የማግኘትና ሰርተፊኬቱን በየዓመቱ የማሳደስ ግዴታ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም የውሻ ባለቤት ለውሻው ማስመዝገቢያና የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ወይም ድጋሚ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፫.ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ውሻውን ለክትባት ሲያቀርብ ውሻው በሶስት ወር ዕድሜውና ከዚያም በኋላ በተሰጠው የክትባት ቆይታ ጊዜ መሠረት የውሻ ዕብደት በሽታ መከላከያ ክትባት ወቅቱን ጠብቆ መከተቡን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፬.ለእያንዳንዱ የተመዘገበ ውሻ አግባብ ያለው አካል ክትባት ይሰጣል፤ ለዚህም ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፭.በእያንዳንዱ ውሻ አንገት ላይ የሚንጠለጠል መለያ ምልክት ወይም ታግ ወይም ኮላር በመጀመሪያው የክትባት ወቅት ይደረጋል፡፡

፮.የውሻ ባለቤት የሆነ አንድ የከተማዋ ነዋሪ ውሻውን ለማምከን ወይም ለማኮላሸት ፈቃደኛ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል፡፡

## PART THREE
## Vaccination and Certification of Dogs Registration

**16. Issuance of Dogs Ownership, Vaccination Certification and Castration**

1. Any person being the owner of a dog as per Article 5 and 6 of this Regulation shall be duty bound to register, issued with certificate of ownership and annually renew the certificate by appearing before the Wereda Trade and Industry Development Office urban agriculture business process when the dog attains three months of age.
2. Any owner of a dog shall pay the service payment required for registration of a dog and ownership certificate or re-issuance of the certificate.
3. When every city's dweller presents the dog for vaccination shall show up evidence of due vaccination for preventing rabies disease at the age of three months and thereafter within the vaccination period given to this effect.
4. Every registered dog shall be vaccinated by the appropriate authority; for which evidence of vaccination shall be consequently been issued.
5. Every dog shall be given a tag to be fixed on its neck or collar during its first vaccination.
6. When any City dweller winning to castrate his dog can get the service by approval of the concerned body.

**፲፯.የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ ለውሾች የሚሰጥ መከላከያ ክትባት**

፩.በአንድ የከተማዋ አካባቢ የውሻ ዕብደት በሽታ ሲከሰት ወይም ሲጠረጠር በእንስሳት ጤና አገልግሎት ሠራተኛ የመከላከያ ክትባት ዘመቻ ያዘጋጃል፡፡

፪.ሁሉም ዕድሜያቸው ከሶስት ወር በላይ የሆናቸው ውሾች ቢሮው ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያወጣው ማስታወቂያ መሠረት የውሻ ዕብደት በሽታ መከላከያ ክትባት መከተብና በተወሰነ ጊዜም ተከታታይ ማጠናከሪያ ክትባት ማግኘት አለባቸው፡፡

፫.የመከላከያ ክትባቱ የሚሰጥበትን ጊዜና ቦታ በሚመለከተው አካል ይወስናል፡፡

፬.የውሻ ባለቤቶች ውሾቻቸውን በተባለው ጊዜና ቦታ እያቀረቡ ማስከተብ አለባቸው፡፡

፭.ውሾች መከላከያ ክትባት ሲከተቡ መከተባቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ይሰጣቸዋል፣ በአንገታቸውም ላይ ልዩ መለያ ምልክት ይደረጋል ወይም ይንጠለጠላል፡፡

**፲፰. ተልከስካሽ ውሾችን ስለ መያዝና ማስወገድ**

፩.ቢሮው ከፖሊስና ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር በቅድሚያ አስፈላጊውን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለህብረተሰቡ ከሰጠ በኋላ ማንኛውም ሲዘዋወር የተገኘ ተልከስካሽ ውሻ እንዲገደልና እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፪.ማንኛውም ለመያዝ አስቸጋሪ የሆነ ተልከስካሽ ውሻ በተገኘበት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፫.ተልከስካሽ ውሻ ለመያዝና ለማስወገድ ስልጣን የተሰጠው አካል በማናቸውም ሁኔታ ተልከስካሽ ውሻን መያዝና ማስወገድ ይችላል፡፡

፬.የተገደሉ ተልከስካሽ ውሾችን ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ፣ በአግባቡ ለመቅበት ወይም ለማቃጠል ቢሮው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡



**17. Dogs Vaccination to be Given in the Area of Rabies Occurrence**

1. When rabies has been occurred or suspected in a certain section of the City, the appropriate authority shall prepare prevention vaccination campaign.
2. All dogs which are attaining more than three months of age shall be vaccinated against the disease of rabies as per the notice issued by the Bureau or concerned authority and also get continuous supportive vaccination within the period set for to this effect.
3. The venue and time for giving prevention vaccination shall be decided by the appropriate authority.
4. Owners of dogs shall get vaccination of the dogs at the said time and place.
5. The dogs getting vaccination shall be issued with evidence of vaccination and also be identified by the special tag worn around their necks.

**18. Catching and Avoiding of Wandering Dogs**

1. The Bureau incollaboration with the police and other Governmental organs shall give the necessary precaution for hunting and avoiding any wondering dog in the area.
2. Any stray dog which being difficult for catching shall be avoided at its whereabouts.
3. An entity given authority to catch and avoid stray dogs can catch and avoid seray dog in any circumstance.
4. For the purpose of collecting, transporting, properly burying or incinerating stray dogs, the Bureau shall jointly work with the concerned bodies.

፭.ሲልከሰከስ ለተወገደ ውሻ ባለቤት ካሳ አይከፈልም፡፡

፲፱. <u>የውሻ ባለቤት መብትና ግዴታ</u>

፩. መብት

ሀ.ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ውሻን በባለቤትነት የመያዝና የማሳደግ መብት አለው፤

ለ.አንድ የውሻ ባለቤት ውሻውን ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት አሳልፎ የመስጠት፣ ውሻውን በሚፈለግበት ጊዜ በማመለከተው አካል እንዲወገድለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

፪. ግዴታ

ማንኛውም የውሻ ባለቤት፡-

ሀ.የውሻ ባለቤት ለመሆን ባለውሻው ውሻው በሚገኝበት ወረዳ የንግድና ኢንዱስትሪ ከልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ውሻውን ይዞ በመቅረብ አስመዝግቦ የባለቤትነት ማስረጃ መያዝ አለበት፤

ለ.ውሻውን በየአመቱ ማስከተብ አለበት፤

ሐ.ውሻውን በይዞታው ስር አድርጎ ጤናውን፣ አመጋገቡን እና አያያዙን መንከባከብና መከታተል አለበት፣ በጨማሪም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በአግባቡ አስሮ መያዝና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፤

መ.ውሻውን ከተመዘገበበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ሲያዛውር ቀድሞ በተመዘገበበት ወረዳ የንግደና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት መልቀቂያ በመውሰድ በተዛወገበት ወረዳ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ማስመዝገብ አለበት ፤

5. No compensation shall be paid to the owner of a dog that is avoided while wandering around.

**19. <u>Rights and Obligations of Dog Owner</u>**

**1. Right**

a. Any resident of the city shall have the right to keep and bring up a dog;

b. a dog owner shall also have the right to transfer his dog to another person or an organization and request the concerned body to terminate the dog when he is no longer in need of the dog.

**2. Obligation**

Any dog owner:

a. Shall be required to appear with the dog before the Wereda Trade and Industry Development Office urban agriculture business process and cause its registration and obtain ownership certificate;

b. Annually vaccinate the dog;

c. keep the dog under his control; follow up the feeding, and the handling, and the care given to the dog; moreover, the owner is required to chain the dog and avoid any injury that the dog may inflict on other people and control it to this effect;

d. Required to obtain a release letter from the former Wereda Trade and Industry Development Office urban agriculture business process where the dog was registered when the dog move from the address where it was registered to another address;

ሠ.ውሻውን በውሻ ዕብደት በሽታ ከተለከፈ ባለቤቱ ኃላፊነት ስላለበት በአካባቢው ለሚገኘው የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ወይም ለፖሊስ ወይም ለጤና ባለሙያ ማሳወቅና ቀጣይ እርምጃ ማስወሰድ አለበት፤

ረ.ውሻው ሲሞት እንዲቀበር በማድረግ ለማዘገበው ወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት በማሳወቅ ከመዝገብ ማሰረዝ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## የአስፈፃሚ አካላት ስልጠንና ተግባር

**፳.የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ**

፩.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭፣ ፮፣ ፯(፩)፣ ፰፣ ፱ የተቀመጡትን ተግባራት ያከናወናል፡፡

፪.ያልተከተቡ ውሾች ሲገኙ እንዲወገዱ ለክፍለ ከተማ ወይም ለወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፡፡

፫.ባለቤት ያላቸው ውሾች በወቅቱ እንዲከተቡና እንዲመዘገቡ ያደርጋል፡፡

፬.ውሾቻቸውን ያላስከተቡ ባለቤቶች እንዲያስከትቡ ያደርጋል፡፡

፭.በመከላከያ ክትባት ዘመቻ ወቅት ሕብረተሰቡ ውሾችን እንዲያስከትብ ቅስቀሳ ያደርጋል፡፡

፮.በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ውሾች መመዝገባቸውንና መከተባቸውን፣ መለያ ቁጥራቸውንና ሰርቲፊኬት በማየት አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

**፳፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ማስወገድ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት**

፩.ለተወገዱት ውሾች የማንሻና ማቆያ ቦታ ያዘጋጃል፤

e. If the dog is infected by rabies, the owner shall bear the responsibility, he is required to report the incident to Wereda Trade and Industry Development Office urban agriculture business process or to the Police or to health professional and take the necessary subsequent action;

f. Buried the dog if died and undertaking the cancellation of registration of the dog by informing the situation to the Wereda Trade and Industry Development Office urban agriculture business process.

## PART FOUR
## Powers and Functions of the Executive Bodies

**20. Addis Ababa Trade and Industry Development Bureau**

1. Perform the activities stated under Articles 5, 6, 7 (1), 8 and 9 of this Regulation.
2. Inform the Sub-City or the Wereda Trade and Industry Development Office for avoiding unvaccinated dogs.
3. Cause timely vaccination and registration of dogs that have owners.
4. Shall make dog owners to vaccinate their dogs.
5. Mobilize the community to bring their dogs for vaccination during preventive vaccination campaign.
6. Inspect the identification numbers and certificates of the dogs in the Woreda Trade and Industry Development Office and ensure that they have been registered and vaccinated.

**21. Solid Waste Recycling And Discarding Project Office**

1. Shall prepare pick up and collection center for terminated dogs;

፪.ለተወገዱ ውሾች ማጓጓዝ የተዘጋጁ ገንዳዎችን በየዕለቱ በማንሳትና ወደ ማዕከላዊ የቆሻሻ መጣያ ቦታ በማጓጓዝ እንዲቀበሩ ወይም እንዲያጠሉ ያደርጋል፡፡

**፳፪. <u>የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን</u>**

፩.ተልከስካሽ ውሾች በሚወገዱበት ወቅት በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋል፡፡

፪.ለማስወገድ አስቸጋሪ የሆኑ ውሾችና ሌሎች በበሽታው የተጠቁ እንስሳት ሲገኙ በአስወጋጅ ባለሙያዎች የእገዛ ጥያቄ መሠረት በጋራ በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

፫.ውሾቻቸውን ለማስከተብ ወይም ለማስመርመር ወይም ለማስወገድ ፈቃደኛ ያልሆኑ ወይም ለማስወገድ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያቀርበው መሠረት ለመቅረብ እምቢተኛ የሆኑ የውሻ ባለቤቶች በማስገደድ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

**፳፫. <u>የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ</u>**

፩.ሰውንም ሆነ ማንኛውም የቤት እንስሳት በነከሱ ውሾች ላይ ምርመራ ያስደርጋል፣ የጤንነት ማረጋገጫ ይሠጣል፡፡

፪.በውሻ የተነከሱ ሰዎች በወቅቱ በአቅራቢያቸው ህክምና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፫.በውሻና ድመት ሕክምና ላይ ለተሠማሩ ባለሙያዎች የቅድመ መከላከያ ክትባት ይሰጣል፡

2. Shall cause daily pick up and transporting avoided dogs to the central west collections area by using west collector tankers that have been prepared for this purpose and have their bodies buried or incinerated.

**22. <u>Addis Ababa Police Commission</u>**

1. Shall provide the necessary protection cover for the employees engaged in the work of avoiding stray dogs at the time of terminating them.
2. If dogs that are difficult to avoid are encountered and animals that are caught by the disease are found, they shall be terminated by joint effort based on request for assistance that may can from avoiding professionals.
3. Shall force the dog owners to appear before the appropriate authority if they are not willing to have their dogs vaccinated or examined or who refuse the termination of their dog or who decline to appear before the authority.

**23. <u>Addis Ababa Health Bureau</u>**

1. Shall cause examination of dogs that may bite human being or any domestic animals (pet); and issue health certification.
2. Shall cause the people bitten by dogs to get timely health care by the nearest health station.
3. It shall give prophylactic vaccination to animal health expert who are engaged in treatment of dogs and cats.

**፳፬. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት**

ያልተከተቡ ውሾች ቁጥጥር፣ እና እርምጃ አወሳሰድ ላይ ከቢሮው ጋር ተባብሮ ይሰራል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፭.ቅጣት**

አግባብ ባለው ሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩትን የተላለፈ ማንኛውም ሰው እንደሆነ ከብር ፩ሺ እስከ ፪ሺ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፳፮.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፯.መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቢሮው ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፰. ተፈፃሚነት ስለሚይኖራቸው ሕጐች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፯**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**24. Office of Code Enforcement Service**

Shall work in collaboration with the Bureau on follow up and control of unvaccinated dogs.

## PART FIVE
## Miscellaneous Provisions

**25. Penalty**

Any person who violates the provisions of this Regulation shall be punishable with 1000 up to 2000 Birr fine unless a higher penalty is provided under the appropriate law.

**26. Duty to Cooperate**

Any person shall be duty bound to cooperate for the implementation of this Regulation.

**27. Powers to Issue Directive**

The Bureau may issue directives for the implementation of this Regulation.

**28. Inapplicable Laws**

Any Regulation, directive or customary practice which is inconsistent with matters covered by this Regulation shall have no effect.

**29. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of 19th day of December, 2014.

**Done at Addis Ababa,**

**On this 19th Day of December, 2014**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**